# ለ 27 ዓመታት በየአላችሁበት ባዕዳን አገራት- የህወሃት/ወያኔ አፓርታይድ ሥርዓት በጽናት ለታገላችሁ ኢትዮጵያውያን ሁሉ !!!

# ፤ ወደ አለንበት ባዕዳን ሀገራት ስለሚሸሹ ወንጀለኛ ወያኔዎችና ተለጣፊዎቻቸው ምን እያሰብን ነው ??

*ወለተማርያም ጋራሞ*

**21/06/2018**

ነገደ እስራኤሎች (Jews) እንደ ማንኛውም ማኅበረሰብ የሚወራላቸው ጥሩ ጎኖችና የሚወራባቸው መጥፎ ጎኖች አሏቸው ።ከሚወራላቸው ፣ከሚደነቁበት ፣በኔም የዕድሜ ዘመን ከማውቅላቸው ጠንካራ ጎኖቻቸው አንዱ - የዜጎቻቸውን ጥቃት ፣በደል ግፍ ፣ስቆቃ ወዘተር.. ተበቃይ መሆናቸው  ነው ። ዜጎቻቸውን-አሳሪ ፣ገራፊ ፣ገዳይ ወዘተርፈ በሄደበት/በሄደችበት ከየትኛውም ክፍል ዓለም አሳደው ይዘው ለፍርድ ያቀርባሉ ፣ያ ማድረግ ካልቻሉ በረቀቀ ዘዴ  በተገኘበት/በተኘችበት ይገላሉ ።

በሁለተኛው የዓለም ጦርነት ሂትለር መራሹ የናዚ ፓርቲ- አምስት <5> ሚሊየን- ረሺያዎችን ፣ፖሊሾችን  ፣ጂፕሲዎችን ፣ ጥቁሮችን ፣ጌዎችን ፣ቄሶችን ፣አካለ-ስንኩላንን ፣ኮሚኒስቶችን ፣የሠራተኛ ማኅበራት መሪዮችን ፣ጀሆቫዎችን ፣እስላቪኮችን ወዘተ.. እና ስድስት <6> ሚሊየን ጅዎችን (Jews) መግደሉን በተለያዩ የታሪክ መጽሃፍት ተጽፍዋል ።ሂትለር እ.ኤ.አ April 30 ,1945 ራሱን በመግደል መሸነፉን ካበሰለበት ዕለት ጀምሮ ፣የሂትለር ቀኝ እጅ የነበሩትን ባለሥልጣናት ወደ ተለያዩ አገራት ሸሹ ። ወደ ሌላ ሃገራት የሸሹትን ሳይጨምር ፣9000 እጅግ በጣም ጨካኝ ጸረ-ሕዝብ የሂትለር መሳሬዎያች ወደ ደቡቡ አሜሪካ ፈረጠጡ ፣በተለይም ወደ - አርጄንቲና ፣ቺሊ ፣ብራዚል ፣ሜክሲኮ ፣ኤልሳልቫዶር ወዘተ..

እስራኤልአውያን May 14,1948  - አገረ እስራኤል (State of Israel) ካውጁበት ዓ.ም ጀምሮ ፣ ወገኖቻቸውን ማለት የነገደ እስራኤል አባላትን -ያጠቁ ፣ያሰቃዩና የገደሉ ናዚዮችን እያደኑ ለፍርድ አቀረቡ ፣እያቀረቡም ነው ። ለምሳሌ የሂትለር መሲና ውሻ <top dogs ከነበሩት አንዱ አዶልፍ ኤክማን (Adolf Eichman) እ.ኤ.አ በ 1960 ዓ.ም አርጄቲና ውስጥ ተይዞ፣ የስራኤሎች ፍርድ ቤት ብስቅላት እንዲቀጣ ፈርዶበት እ.ኤ.አ በ 1962 ዓ.ም ተገደለ።     ይዘው ለፍርድ ማቅረብ ካልቻሉ በተገኘበት/ችበት የሚገሉበት ምክንያት፤

1.የወንድሞቻቸውና የህቶቻችውን -ጥቃት፣ ሰቆቃና ሞት ከንቱ ሆኖ እንዳይቀር ወይም ለመበቀል

2.የሕግ የበላይነት ለማሳየት እና ለሕግ የማይምበረከኩ ግፈኞች ሃይል የሚያስፈልጋቸው መሆንን ለማስተማር

3.ሰው በግፍ ማጥቃት ፣ማስቃየትና መግደል - የመዝናኛ እስፖርት (hunting for leisure) ወይም ሥጋቸውን ለመብላት የዱር እንስሳት ማደን ( hunting animals in the wild for their meat)እንዳልሆነ ትምህርት ለመስጠት

4. ወደፊትም እንዳይደፈሩ ፣ተፈርተውና ተከብረው እንዲኖሩ ለማድረግ

5. ስለሆነም - አንድም ሆነ ምሊዮን ጅዎች (Jews) - ያጠቁ ፣ያሰቃዩ ፣የገደሉ ወዘተርፈ በየትኛውም የሰው ልጅ መኖርያ ምድር ፣ሥፍራ/ቦታ  እጅግ በጣም ተደብቆ ፣ ፈርተውና ተጨንቀው ፣እንደ አይጥና እንሽላሊት ተሸለኩልኮ ይኖሩ ይሆን እንጂ ፣ ተዝናንተውና አደባባይ ወጥተው አይኖሩም/ኖርም/ትኖርም ።

እኛ ኢትዮጵያውያን በሕባችን ላይ አስከፊ ግፍና ወንጀል ከፈጸሙትን ፀረ-ሕዝቦች ጋር ያለን ግንኙነት ምን ይመስላል? አውንታዊ ውይስ አሉታዊ ? ተጻራሪ ወይስ ተቃቃፊ?

በፋሽስቱ መንግሥቱ ሃ/ማርያም የበላይነት የተመራው ፋሽስታዊው የደርግ ሥርዓት ዕድሜ አጠናክረው ለማራዘም ፦ አባቶቻችንን ፣እናቶቻችንን ፣ወንድሞቻችንን ፣ እህቶቻችንን፣ ጓደኞቻችንን  ወዘተርፈ - ከገረፉ ፣ካሰቃዩ ፣በሰቆቃ የወንድና የሴት ብልቶቻቸውን ዘር እንዳያፈራ ካደረጉ  ፣አካለ ስንኩል ካደረጉ፣ በገፍ ከረሸኑ የሰው አውሬ **<beasts>** የደርግ ካድሬዎችና ለደርጊቱ ትእዛዝ የሰጡትን ባለሥልጣናት ፣የቆሙለትን ሥርዓት ሲንኮታኮት ፣ ሰቆቃና ሞትን ሸሽተን ወደ ምንኖርባቸው ፣ ባዕዳን አገራት ሲመጡ ፣ለፈጸሙት ግፍ ፣ወንጀል፣ክህደት፣ኢሰብአዊነት ወዘተ..መቀጣጫ እንዲሆን ምን የወሰድነው እርምጃ ነበር?      አለ?

ከሶስት ሳምንታት በፊት ጠ/ምኒስተር አብይ አህመድ ምኒስተሮቻቸውን ሲያሰለጥኑ/ኢንዳክት ሲያደርጉ 23,000 የቀይሽብር ተሳታፊዎች በባዕዳን አገራት እንደሚገኙ ጠቅሷል ። ይህ ቁጥር ከየት አገኙት? የሚል ጥያቄ በአእምሮዋችን ይጉላላ ይሆናል ። የአሁኑ ጠ/ም በወያኔ ቋንቋ የትላቱ የሕዝብ ደኅንነት ፣ በእኔ ቋንቋ የትላንቱ የሕዝብ አጥፊነት መሥርያ ቤት ቁንጮ ሰው ስለነበሩ ፣የደርግ የቅይሽብር ካድሬዎች የነበሩትን የተመዘገቡበትን መዝገቦችን/ፋይሎችን አግኝቷል ማለት ነው ።ከነዚህ ወስጥ ሦስት  ጸረ-ሕዝብ ካድሬዎች ብቻ ማለት ሁለቱ በአሜሪካ አንዱ በአውሮጳ  ተይዘው መታሰራቸውን አውቃለሁ ፤ ማለት 23,000 – 3 = 22997 ዎቹ ጋር ፦

- አብረን - ቁርጥ ሥጋና ክትፎ እየበላን ፣አብረን ውስኪ እየጠጣን ፣አብረን እየጨፈርን/እየደነስን   ወዘተ.. እንኖራለን ፣የዚህ ዓይነት ባህል አዳብረናል።

  እነዚሁ ፀረ-ሕዝቦች ፣ድርብ ፀረ-ሕዝብ በመሆን ፦

- እንደገና መወለድ በ<born again> ቤተክርስቲያናት አባልና ፓስተር በመሆን  - መንግግሥት እግዜር ያመጣዋል ፣እግዜር ይሽረዋል ፣ስለሆነም ወያኔ አታውግዙ ፣አትቃወሙ እያሉ ሲሰብኩ ፤ አገር የለንም ፣ አገራችን የሰማይ ቤት ነው እያሉ ሲሰብኩ ይደመጣሉ
- በአፍቅሮተ ወያኔ ኦርቶዶክስ ቤተክርስቲያናት ተሰግርተው -የወያኔ የሥልጣን ዘመን እንዲራዝም ሲፀሊዩ ፣ሲያጠናክሩና ድጋፍ ሲሰጡ ኖሯል
- ከወያኔ ኢምባሲዎችና ፣ቆንሱላት ሠራተኞች ጋር በመለጠፍ ፦<1> የአባይን ግድብ መስሬያ  <bond>አራጣ አበዳሪዮችን <2> በአገር ቤት ወያኔዎች በሚፈልጉት አካባቢ       የሚያለሙትን/ንግድ የሚከፍትቱን ዲያስፖራዎችን አደራጅቷል ፤ቀስቅሷል ። አገር ቤት እየተመላለሱ ኢንቬስት አድርገዋል ፣ህንጻ ቤቶች አሰርተው አከራይተዋል
- በዘመነ ወያኔ በአገር ቤትም ሆነ ከአገር ውጭ እንደ እንጉዳይ ብቅ ብቅ ባሉትን ተቃዋሚ የፖለቲካና የሲቪል ድርጅት ተብዮች ወስጥ ተሰግስገው ወያኔን አገልግሏል
- በዘመነ ወያኔ እንደ አንበጣ የተፈለፈትን -የዲስፖራው ሚዲያ ቷናይ ሆኖዋል

- ቁጥራቸው ጥቂት ቢሆንም ፣ በጸረ-ወያኔ ኦርቶዶክስ ቤተክርስቲያናትም ውስጥ እንዳሉ ይስተዋላል፣እንደውም -መቋሚያ ይዘው ከሚያሽበሽቡትን ምዕምናን ጋር በመሆን በበጎች መካከል ለምድ የለበሰ ቀበሮ እንደሚባል ዓይነት ሲያስመስሉ ይታያሉ

ሀ/ ከ 500,000 በላይ ፦

- ምጥቅ ማኅበራዊ ፣ፖሊቲካዊና ኢኮኖሚያዊ ንቃተ ኅሊና የነበራቸው ፣በሕዝባቸውና በሀገራቸው ፍቅር የሰጠሙ ፣ፍጹም ጀግናና የኢትዮጵያ አለኝታ የነበሩ - ወጣት ፣ጎልማሳና አዛውንት ምሁራንን በጥይት አስመትሮ፣ሬሳቸውን ሽጦ ፣ወላጅና ቤተሰብ እንዳያለቅስላቸው ከልክሎ/አሳገዶ -ከፍተኛ ምሁራዊና ምርጥ ወታድራዊ ችሎታ የነበራቸው መኮንኖችን በመትረየስ አሳጭዶ እና በአንድ ጉድጓድ ቀብሮ

-በካድሬዎቹ አቃጣሪነት - ከብዙ ዓመታት የአካዳሚክ ትምህርት፣ የውትድርና ልፋትና ብቃት በኋላ ያገኙትን ማዕረግ ፣ወደ ተሰማሩበት የጦር ሜዳ ድረስ በመሄድ ፣ በሚያዙትን ሠራዊት ፊት - ከትከሻቸው ላይ በመቀስ በመቁረጥ ፣በጥፊ በመምታት ፣ እዛው በጥይት በመድፋት ወዘተ..አዋርዶና ቅስማቸውን ሰብሮ - ኢትዮጵያና የኢትዮጵያ ሕዝብ ከጠላት የሚከላከልለት - ደፋርና ጀግና ዜጋ ከኢትዮጵያ ምድር አጥፍቶ/መንጥሮ፣የአገራችንን መልካአ-ምድር ለወያኔዎች አመቻችቶ ወደ ዚምባቦይ የሸሸው ፣ሰው በላው (cannibalist) መንግሥቱ ሃ/ማርያም

ከላይ ላስጨብጥ እንደሞከርኩት ፦ ያ (በዘመናዊ ውትድርና እውቀት ፣በዘመናዊ ትምኅርት ፣በዘመናዊ ንቃተ-ኅሊና ወይም አስተሳሰብ የላቀው ፣በአገርና በሕዝቡ ፍቅር የሰመጠው ፣በአገሩና በሕቡ ጥቅም ከባዕዳን ጋር ያልተደራደረው ፣ ጀግናና አርበኛ ትውልድ) በፋሽስቱ መንግሥቱ ትእዛዝ - በክላሽኮቭ ፣በሎዚና በመትረየስ ባይታጨድ/ባይመነጠር ኖሮ ፣ ወያኖች ከትግራይ ክልል አይወጡም ፣አይወሩንም፣ አይገዙንም ወዘተርፈ ነበር ። የኤርትራ መገንጠል ፣የአሰብና የምጽዋ መወሰድ እና የወያኔዎችም ኢትዮጵያን ለመውረር መሠረት የጣለውና ያመቻቸው መንግሥቱ መራሹ ድርግ ነው ባይነኝ ። ወያኔዎች በተነጠፈላቸውን አዳራሽ ነው የጨፈሩት ። ፋሽስቱ መንግሥቱ ለሻቢያና ለወያኔ የሚሰልሉ/የአገር ህልውናን የሚፈታተኑ ሚስጥሮችን የሚያቀብሉ የደርግ አባል/አባላት በጉያ ሥር መኖራቸውን እያወቀ ወደ ዚምቧቤ እስከ ፈረጠጠበት መጨረሻው ሰዓት ድረስ አቅፏቸው/ይዟቸው ተጓዘ ።

ፋሽስቱ መንግሥቱ ሃ/ማ በጣም ያስጨንቀው የበረው የኢሕአፓን እንቅስቃሴ እንጂ ወያኔዎችን አልነበረም ። የሠራዊቱን ትኩረት ሁሌ ኢሕአፓ ላይ እንዲሆን ትእዛዝ ይሰጥ ነበር እንጂ ወያኔዎችን መቱ/አጥቁ አልነበረም ። ይህ ማለት ወያኖች መንግሥቱ ለኢትዮጵያ ሕዝብ ያበረከታቸው ፣ በረከቶች/ስጦታዎች ናቸው ።ፋሽቶቹ ደርጎች ወያኔዎችን በካድሬነት በመቅጠር ጭምር ነው ኢሕአፓዎችና ሌሎች ዲሞክራት ዜጎችን ያስጨፈጨፉት።

ለ/ ለአሜሪ የስለላ ድርጅት <C I A> እና የሻቢያ ቅጥረኛ በመሆን የሉዓላዊነታችን ሚስጥር አሳልፎ የሰጠው ፣በመንግሥቱ ሃ/ማርያም ላይ ታቅዶ የነበረውን መፈንቅለ መንግሥት እንዳይሳካ ሚስጥር ለመንግሥቱ ሹክ ያለው - ሻለቃ ዳዊት ገብረጎርጊስ በምሳሌነት ማቅረብ ይቻላል። እኚህ ፀረ-ሕዝብ የባዕዳን ቅጥረኛ ፦ ለማኅበራዊ ፍትኅ ፣ለሕግ የበላይነት ፣ለመልካም አስተዳደር ፣ለብሄር ብሄረሰብ እኩልነት ፣በሰላማዊ መንገድ ለግዜያዊ ሕዝባዊ መንግሥት መመሥረት ወዘተ.. በመታገላቸው **<1>** እንደቁራ በሬ የታረዱትን የለውጥ አርበኞችን **<2>** ከዚያ የጭፍጨፋ ምትራ አምልጠው የፀረ-ወያኔ ትግል መሠረት የጣሉትን እውነተኛ የኢትዮጵያ ልጆች- ሲከስና ሲወነጅል ይደመጣል ።

ሐ/ በግማሽ ሚሊዮን - እንቡጥ ወጣቶችን ፣ወጣቶችን ፣ጎልማሶችን ፣ አዛውንቶችን ፣አረጋውያንን ላይ ቀይሽብር ወይም ህግ አልባ ረሸና/ጭፍጨፋ እንዲፈጸምባቸው የፈረሙትን እነ-ፍቅሬ ወግደረስ እና ፍሳሃ ደስታ

መ/ ለዘመናት በመልካም በጉርብትና የኖሩ ፣ተጋብተው የተዋለዱ ፣ሃዘናቸውንም ደስታቸውንም የተካፈሉ ፣ያገኙትን አብረው የበሉና የተቃመሱ፣ጥንታዊ ትውልደ ኢትዮጵያውያን ፣ ተስማምቶ እንዳይኖሩ ፤ አገራችን በጎሳ ታርጋ ፌደራሊዝም ወይም ክልል እንዲተዳደር የመከረው ፤የወያኔዎች ሻንጣ ተሸካሚው ሌንጮ ለታ

ሠ/ የሃይማኖት አባቱ አቡነ መርቆሪዮስን እንዲሰደዱ ያደረገው ፣ኦሮሞችን በአማራ ላይ እንዲዘምቱ ፣አማራን እንዲገሉ የቀሰቀሰው ፣ከህወሃት መሲና ውሾች <top dogs> ከነበሩት አንዱ ታምራት ለዓይኔ አይነቶች በተደጋጋሚ በ(EAST,SBS,VOA ETC. መዲያ ጋዜጠኞች እየቀሩቡ ፣የአገራችንን ተጨባጭ የፖለቲካ አድማስ እንዲመከሩና እንዲያስረዱ ለቃለመጠየቅ ሲፈልጓቸው ፣እንደ የኢትዮጵያ ጀግኖች፣ የኢትዮጳያ ባለውለታዎች ፣የኢትዮጳያ ዕንቁና የተከበሩ ልጆች ወዘተ.. እንደሆኑ አድርገው ሲያስተናግዷቸው **(As if they are heroes and legendaries of Ethiopia**) ስከታተል፦

- እነዚህ ጋዜጠኞች ሁሉ የደርግ ካድሬ እንደነበሩና የወያኔም ሥውር ካድሬ እንደሆኑ ይስማኛል/ እገምታለሁ
- የኢትዮጵያና የኢትዮጵያ ሕዝብ ፍቅር እንደሌላቸው ያሳያሉ
- በእነዚህ ፀረ-ሕዝቦች <people`s enemy> ምክንያት እቤታቸው -ሰቆቃ ፣ሞትና ሃዘን እንዳልገባ ያሳብቃሉ
- ስብዕና የሚባል ነገር አእምሯቸውን እንዳልዳሰሰው ያስመሰክራሉ

ከላይ ልጠቁማቸው የሞከርኩትን የለየላቸው ፦ ፀረ-ሕዝቦችን፣ ወንጀለኞችን፣ የሉዓላዊነታችንን ሚስጥር ላባዕድ የሸጡ ፣የሲአኤ <C I A> ቅጥረኞችን ፣ ጎሳን በጎሳ ላይ አስነስቶ ዜጎቻችንን ያስጨፈጨፉትን ፣ትውልድን የመተሩና በወገኖቻችንን እሬሳ ላይ የነገዱትን ፣አገራችንን ለመቆራረስ የዳከሩትን ፍጹም ባንዳዎችን በማስተናገድ ፤ በምን እንደሚሞሉት የሚያስጨንቃቸውን የከፍያ ሰዓታቸውን ያሚሉበታል።

ከዚህ ገጽ በጣም ከፍ ብዬ እንደገለጽኩት ፣ እነዚያ ሶስተኛው የተማረው ባለ ብሩህ አእምሮ ትውልድ ፦የቀጠፉ፣የመተሩና የገደሉ ደርጎችና ውሾቻቸው ላይ ምንም ዓይነት እርምጃ ያልወሰድነው ፣ተባብረንና ተቃቅፈን የምንኖሮ ፣እነሱ ሲንኮታኮቱ ወዲውኑ ደርጎች ያከሰሙትን፣ያዳከሙትን፣ያሸበሩትን አገራችንና ሕዝብችንን ድብን አድርገው በሚገሉ ወያኔዎች ስለተተካ ይመስለኛል።ደርጎችና ደቀመዛሙርቶቻቸውን መበቂያ ግዜ አላገኘንም ።

ማድረግ የነበረብንና ወደፊትም ማድረግ የሚኖርብን

ሀ/ሃቀኛና የመደብ ጀርባውን/ጅርባቸውን ሕዝባዊ በሆነ/በሆኑ ግለስብ ወይም ቡድን አነሳሽነት ፤

- በሁሉንም ኢትዮጵያውያን በሚኖሩባቸው ባዕዳን ሃገራት ዋና ዋና ከተማዎች ሥውር ኮሚቴ ማቋቋም
- በሁሉንም በዕዳን ሃገራት ዋና ዋና ከተማዎች የተቋቋሙትን ኮሚቲ ተጠሪዮች ጋር የሥውር ግንኙነት መፍጠር

-በየትኛውም ኢትዮጵያውያን በሚኖሩባቸው ከተሞች በጸረ-ዝብነት የሚጠረጠር የምትጠረጠር ሲገኝ/ስትገኝ (ሙሉ ስሙ/ስሟ እና ፎቶግራፍ) በሁሉንም ባዕዳን ሃገራት ዋና ዋና ከተማ ለሚገኙ ኮሚቲ ተጠሪዮች ማስተላለፍ/ መላክ

-የተወለደበት/የተወለደችበት ፣የሥራበት/የሥራችበት አካባቢ ወዝተ.. ማጥናት

- ለተጠረጠሩበት ወንጀል ማስረጃዎች ስብስቦ ለፍርድ ማቅረብ

ለ/ - ከአደባባይ ሕይወት <public life> እና ከማኅበራዊ ሕይወት ማለት -ከዕድር፣ከዕቁብ፣ ከሥርግ ፣ አብሮ ከሙብላትና ከመጠጣት ወዘተ.. ማግለል

-ከማናቸውም በ(TV,paltalk,radio etc) ከሚደረጉ ውይይትና መስተንግዶ ማግለል

-ተዝናንተው ሳይሆን ፣ተሸማቀው ፣ፈርተው ፣ተጨንቀውና ተደብቀው እንዲኖሩ፤ ማኅበራዊ ቀውስ እንዲገላቸው ማድረግ ።

የአርእስቱ መልዕክት የትአለ ? አርእስቱ ሌላ የሚጽፈው ሌላ ፣ "ፍየል ያለው ወዲህ ቅዝምዝም ያለው ወዲያ' ትሉ" ይሆናል። በዘመነ ደርግ በሕባችንና በአገራችን ላይ ከፍተኛ በደል በፈፀሙትን ፀረ-ሕዝቦችና የባዕድ ቅጥረኞች ላይ ምንም ዓይነት እርምጃ አልመውሰዳችን ከዚህ አርእስት ጋር ማዛመድ/ማገናኘት ስለፈለኩ ነው ቶሎ ወደ አርእስቴ መልዕክት ያላመራሁት።

በትላንትናው ቁጭታችን ፣በትላንትናው ድክመታችን ፣በትላንትናው ችለተኝነታችን ወዘተ.. የዜሬውንና የነገውን (አቋማችንን ፣አቅጣጫችንን ፣እይታችንን ውዘተ.. መቀየስ ፣መመርመር ፣ማስተካከል ወዘተ.. ይኖርብናል) ።

"To know the present we must look into the past and to know the future we must look into the past and the present" (Dr Walter Rodney,1982). ጃሜካዊው የፖለቲካ ሳይንስ ምሁር < ዶ/ር ወልተር ሮድኒ> "የዛሬውን ለማወቅ ያለፈውን ማየት ወይም መመርመር፤የመጪውን ወይም የወደፊቱን ለመረዳት ያለፈውንና የአሁኑን ማጥናት" ግድ ይላል ብለዋል።

ወደተነሳሁበት አርእስት ላምራ

ወያኔዎች መግዛት እንጂ መገዛትን ስለማይፈልጉ - ሥልጣናቸውን ተመርኩዘው ወገኖቻችንን :- የገደሉና ያስገደሉ ፣የገረፉና ያስገረፉ ፣ያፈናቀሉና ያስፈነቀሉ ፣አንድን ጎሳ በሌላ ጎሳ ላይ አሳምጸው የብዙኋን ሕይወት ያስቀጠፉ ፣በዳር ድንበራችንና በአገራዊ ሉዓላዊነታችን ላይ ደባ የፈጸሙ ፣ በሄራዊ ሃብታችንን አሟጦ ዘርፈው አገራችችን ፍጹም ድሃ ያደረጉ ወዘተ..ወያኔዎችና ተለጣፊ ወያኔዎች በቦሌ አየር መንገድ መውጣት ካልቻሉ :-በግል መኪናቸው ፣በክራይ መኪና ፣በግመል ፣በበቅሎ ፣በፈርስ ፣በአህያና በእግር ጉዞ ወደ ጎረ ቤት አገራት ሂደው ውፍራም ዶላር በመክፈል ወደ የምንኖርባቸው ባዕዳን አገራት እንደሚመጡ ዕሙን ነው ።

ሥልጣን ከተቆናጠጡበት ግዜ ጀምሮ ልጆቻቸውን፣ ሚስቶቻቸውን፣ እህቶቻቸውን ፣ ወንድሞቻቸውን ፣ ባጠቃላይ ቤተሰባቸውን በተለያየ ሽፋን አስውጥቷል ። በትምህርት፣ በውሸት ስደተኝነት ፣በዲፕሎማሲያዊ ሉዕከነት፣በሞያተኝነት ፍልሰት <skilled migrant> ፣በንግድ ፍልሰት <business migrant> ፣በውሸት ጋብቻ ወዘተ..ሽፋኖች ። በተለይም ካለፉት አራት ዓመታት ወዲህ ከአገር የመውጣት ፍ

ሰታቸው በጣም የጨመረ መሆኑን የምንረዳው በምንኖርባቸው የባዕዳን አገራት ከተማዎች በርካታ አዳዲስ ወያኔዎችና የወያኔ ቤተሰብ ሲርመሰመስ ስለምናይ ።

በቤተሰባቸው ስም -ንግድ ቤቶች፣ የመኖርያና የሚከራዩ ህንጻዎች ተገዝቶላቸዋል ። በሜልቦርን <አውስትራሊያ>- አንድ የወያኔ ባለሥልጣን ቤተሰብ እስከ አምስት በዓይነት የተለያዩ ንግድ ቤቶች ያሏዋቸው ።በዚሁ በሜልበርን በጣም ሃብታሞች በሚኖሩበትና በሚዝናኑበት 'Melbourne Dockland' በመባል በሚጠራው የውክያኖስ ዳርቻ ከተማ በአባይ ወልዱ ቤቴስብ ስም በ **7000,000** የአውስትራሊያ ዶላር ህንጻ ቤት እንድተገዛ በከተማው ከሚኖሩ ኢትዮጵያውያን ይደመጣል፤ ለማጣራት እንሞከራለን ።

በዚሁ በሜልቦርን <አውስትራሊያ> ኬኔዲ በመባል የሚጠራ ትውልደ ትግራይ የሆነ - የሂሳብ ሠራተኛ ማለት የቀረጥ ማወራረጃ ቢሮ <Taxation office> ያለው ሰው አለ ። ይህ ሰው በሜልቦርን ከተማ የወያኔ ባለሥልጣኖች ቤተሰቦች ጉዳይ አስፈጻሚም ነው ። ማለት የቤተስብ መኖሬና የሚከራዩ ህንጻዎች ፣የንግድ ቤቶች ፣ንግዶች ወዘተ.. እየተጫረተ ይገዛላቸዋል ።

ከአራት ወራት በፊት የአውስትራሊያ ኅብረ-መንግሥት (የፌደራል መንግሥት) ፖሊስዎች ወደ ቢሮው/አፊሱ ድረስ በመሄድ ፣ኮምፒተሮቹን በሙሉ በቁጥጥር ሥር አውለው ይዘውበት ሄዱ ።ፖሊስዎች ለድርጊቱ የሰጡት ምክንያት **(money laundry from Africa)** በሕገወጥ መንገድ ከአፍሪካ ገንዘብ ታነጉዳል**/**ታስመጣለህ በሚል እንደሆነ ተነገረ ።

ለመንግሥት ጥቆማ ያደረጉት ኢትዮጵያውያን ሳይሆኑ ፣ነጮች እንደሆኑ ተነገረ ፣ለዚህ የተሰጠው ምክንያት አቶ ኬኔድ ለቤት ግዢ በሚጫረትበት አካባቢ፣ ጫረታዎችን እያሸነፈ ሌሎች ተጫራቾች ከውድድር ውጭ እያደረገ አላስቀምስ በማለቱ ተገርመውና ተበሳጭተው በት ነው የጠቆሙበት ተባለ ።

ጉዳዩ እየተከታተልን ነው ። ይህ ለናሙና አቀረብኩት እንጂ በሌሎችም የአውስትራሊያ ግዛቶች <እስቴትስ> ተመሳሳይ ሁኔታዎች ይደረጋሉ ።አውስትራሊያ ለወንጀለኛና ለሃብታም ወያኔዎች መደበቂያና ምቹ **(save haven)** ኮሆኑ ሃብታም አገሮች አንዱ ይመስላል ።በአው ሮጳ አገሮች ፣በካናዳ ፣በአሜሪካ ፣በደቡብ አፍሪካ ፣በሃብታም መካከለኛ ምስራቅ አገሮች ወዘተረፈ ተመሳሳይ ይሁንታዎች አሉ ።

አዲሱ ጠቅላይ ሚኒስተር አብይ አህመድ 'መንግሥቱ ሃ/ማርያምም ቢሆን ወደ አገሩ ተመልሶ በነጻ መኖር እንደሚችል' ተናግሯል ።ይህ አባባል ፡- መንግሥቱን ለመጥቀም ሳይሆን -ወያኖችን እንዳይከሰሱ ፣ የወያኔዎችን ወንጀል ለማቅለል ወይም ለመሸፈን ካላቸው ፍላጎት ጋር ታስቦ ምህረት የመስጠት ዝንባሌ ይሆናል ቤዬ ጠረጠርኩ ።

ጠቅላይ ምኒስተር አብይ በሚሊዮን ኢትዮጵያውያን ደም የታጠቡ ፣የሚሊዮኖች ኢትዮጵያውያን ህይወት የቀጠፉ ፣በአገራዊ ሉዓላዊነታችንና ኅልውናችን ላይ ከፍተኛ ደባ የፈጸሙትን፡- የደርግ ፣ የወያኔና የኢህዴግ ባለሥልጣኖችን ምህረት የመሥጠት ስልጣን የላቸውም ።ካልተሳሳትኩ የዚህ ዓይነት ምህረት ማድረግ የሚችለው ፤የዲሞክራሲያዊ ሕገመንግሥት አካል በሆነው ዲሞክራሲያዊ የፍትኅ ሥርዓት ወይም በዚህ ሥር በሚቋቋመው የብሄራዊ እርቅ ኮሚሽን ነው ። በደቡብ አፍሪካ በአፓርታይድ ሥርዓት ማብቂያ በማንዴላና በዴዝመንድ ቱቱ መሪነት የተቋቋመውን የእርቅ ኮሚሽንና የፍትህ ክንውን መጥቀስ ይቻላል። ለምሳሌነት ጠቀስኩት እንጂ የእኛዎቹ **(**ደርጎችም ሆኑ ወያኔዎች**)** ፤ የአፓርታይድ ሥርዓት በደቡብ አፍሪካ ከፈጸመው ግፍ እጅግ በጣም የላቀ ግፍ ፈጽሟል ።

እነዚህን ፍጹም አምባገነን፣ፍጹም ጻረ-ሕዝብ ፣ ፍጹም ፅረ-አገር ፣ፍጹም ፀረ-አንድነት ወንጀለኞችና ከሃዲዮች ያለምንም አንጻራዊ ፍርድ ፣ ከሰፈው የኢትዮጵያ ሕዝብ ጋር ተቀላቅላችሁ ኑር ማለት በርካታ አሉታዊ መልዕክት ወይም እንድምታ ይኖሮዋል።ከእነዚህ ጥቂቶቹ ፡-

1. ዊኒ ማንዴላ ለአፓርታይድ ፖሊሶች ሚስጥር ያቀብላ

በማለት አንድ ልጅ በማስገደሏ የገጠማትን ማኅበራዊ ተጽኖና ውግዘት ሰምተናል። ግማሽ ምሊዮን በሚደርሱ የቅይ ሽብር ተጠቂዮች እና ከዚያ ውስጥ እስከ 6 ልጆቻቸውን ባጡ ቤተሰቦች ፡-ሃዘን ፣ ቁስል ፣ህመም ፣ኅዋስ ፣አጥንት፣ ነፍስ/ሶል ፣ሥነ-ልቦና ወዘተ..ላይ ቤንዚን አርከፍክፎ ማጋየት አይሆንምን?

2. የኢትዮጵያ ህዝብ ሥርዓትና ሕግአልባ እንዲሆን ፤ ያራዊት ሥርዓት እንዲከተል አይጋብዝምን?

3. ማኅበረሰባችን ኢ-ግብረገባዊ ፣ኢ-ኅሊናዊ ፣ኢሰባዊ ወዘተ..ባህል እንድያዳብር አይጋብዝምን?

4. በዜጎች ላይ ሰቆቃ መፈጸም ፣ ማሰቃየትና መግደል - እንደ መዝናኛ እስፖርት እየሆነ ሊመጣነው ማለት ነው ።

ብስል/የበለጸገ ዲሞክራሲያዊ ሥርዓት አላቸው በሚባሉ አገሮች እንኳንስ ሰው መደብደብና መግደል ፣ በማኛውም የቤት እንስሳ(ውሻ ፣ድመት ወዘተ..) የምሳሰሉት ያለአገባብ የገደሉና የአካል ጉዳት ያደረሱ 'በእንስሳት ላይ ጭካኔ መፈጸም' <animal cruelty>በሚል በእስራት ወይም በገንዘብ ይቀጧቸዋል ።

5.አገር ማስገንጠል ፣የብሄራዊ ባህር በር ማስነጠቅ ፣ብሄራዊ አንድነት ማናጋት ፣ሕዝባዊ አንድነት መሸርሸር፣ማፈናቀል፣የእርስ በርስ ግጭት መቀስቀስ ፣ በአጠቃላይ በዜጎችና በአገር ሉዓላዊነት ላይ ከፍተኛ ደባና ክህደት መፈጸም ወዘተ..ምንም ዓይነት ዋጋ ላያስከፍል ነውን? የነገው ትውልድ ከዚህ የሚማረው ምንሊሆን ነው ??

በቅርብ ግዜ በአገር ቤት ብሄራዊ መግባባት መድረክ ላይ የኢትዮጵያን ብሄራዊ ፖሊቲካ ይሁንታ ከሌሎች የአፍሪካ አገራት ፖሊቲካ ተዛምዶ ሲነሳ፣ አንድ የቄስ ልብስ ለብሶ በሥፍራው የተገኙ ወያኔ ፣<ኢትዮጵያ ከሌሎች በቅኝ ከተገዙ አገሮች ይሁንታ ጋር አታዛምዱ ፤እኛ ጋ የሆነው በወድሞቻችሁ ነው ፣ስለሆነም ቂም አትያዙ ዓይነት> ሃሳብ ሰነዘሩ ።እኚህ ሰው ወያኔዎች በአገራችንና በሕዝባችን ላይ ያን ያህል ግፍ ሲፈጽሙ ፤ተው በአገራችሁና በሕዝባችሁ ላይ ግፍ አትፈጽሙ ለምን አላሉም?? የማይጠገን የአእምሮ ጠባሳ የሚሆነው የወገን ጥቃት እንጂ የጠላት ጥቃት አይደለም ።በገዛ ወንድሙ ስለተገደ ዘመድ ሃዘን ነው ወይስ በባዕድ ስለተገደለ ዘመድ ሃዘን የበለጠ ሚሰማን**?** ፍረዱት**!**

ስለሆነም እነዚህን አሳድዶ ለፍርድ ለማቅረብ ያለን **-**ስነልቦናዊ ፣ቁሳቁሳዊ ፣ድርጅታዊ ፣ሞያዊ**<** ማለት ሕጋዊ እውቀት**>** ወዘተርፈ ዝግጅት ምንያህል ነው **?** ወይስ ከዚህ ቀደም እንዳደረግነው **-**አብሮ መብላት ፣አብሮ መጠጣት ፣አብሮ መጨፈር ፣መተቃቀፍ ፣አብሮ መተኛት ነው የሚሆነው ? ይህንን ሃሳብ የምትወዱትም የምትጠሉትም እንዳላችሁ እገምታለሁ ፤ እኔ ግን እንድ አንድ አገሬና ሕዝቤ ወዳድ ኢትዮጵያዊ- የሚታየኝና ይሚሰማኝን -ማካፈሌ ፣ማገናዘቤ ፣ማሳሰቤ ፣ማመላከቴ ወዘተርፈ

በቅርብ ግዜ በአገር ቤት ብሄራዊ መግባባት መድረክ ላይ የኢትዮጵያን ብሄራዊ ፖሊቲካ ከሌሎች የአፍሪካ አገራት ፖሊቲካ ተዛምዶ ሲነሳ፣ አንድ በሥፍራው የተገኙ ቄስ ፣<ኢትዮጵያ ከሌሎች በቅኝ ከተገዙ አገሮች ይሁንታ ጋር አታያይዙ ፣እኛ ጋ የሆነው በወድሞቻችሁ ነው ፣ስለሆነም ቂም አትያዙ ዓይነት> ሃሳብ ሰነዘሩ ።